ፊት አብራርቶና አንጠርጥሮ ተናገር የሚያስምንበት አላማና ፕሮግራም የሌለው፤ ግን በሌላው አ ያም ተራማጅ ክብሉ ለማለፍ የሚፈልግ ኦፖርቹኒ መሆን አለበት፡፡ወይ ደግሞ እንከን የለሽ ፕሮግራምና አላማ ኖሮት ያንን ያለሰፊው ህዝብ ተሳትፎ ጥቂት ''የምስጢሩ ተካፋዮች'' ጋር ሆኖ አላማውን እውነታለሁ የሚል ከ ሃሳብ ብቻ የሚመዘቅ ሃሳባዊ /አይዲያሊስት/ መሆን አለበት፡፡ የፊተኛው በራሱ እምነት የለውም፡፡ ሁለተኛው በሰፊው ህዝብ እምነት የለውም፡፡ ሁለቱም ለአብዮት አይረቡም፡፡መሲሁን ግን በራሱም ሆነ በሰፊው ህዝብ ይተማመናል፡፡ትክክለኛ አላማ አለኝ ብሎ ያምናል፡፡ግን ደግሞ ይህ አላማ ቢህ ጊዜ ትክክለኛ ቢሆን በሚሊዮን የሚቆጠረው ሰፊ ህዝብ አምኖበት ካልተከተለውና ካልተዋጋለት ከስራ ላይ እንደማይውል ያውቃል፡፡ በማርክስ አነጋገር ትክክለኛ ሃሳቦች ወደ ተጨባጭና የማይበገር ሃይል የሚለወጡት በሚሊዮን በሚቆጠሩ ህዝቦች አእምሮ ሲታነፁ ብቻ ነውና፡፡

ስለሆነም ግቡን፤ ፕሮግራሙን፤ የትግል ስልቱን፤ ወዘተ... በግልፅ ራሱን ለማስተዋ ወቅ ይታገላል፡፡ይህ ደግሞ በሰፊው ህዝብና በራሱ እምነት እንዳለው የሚያሳይበት አብዮታዊ ድርጊት ነው፡፡

የአድሃሪው ቢሮክራሲ ሴራ ይከሽፋል!

አድርባዮች አ ያም ተቱ አሉባልታ ሲነዙ ይጋለጣሉ!

አሉባልተኞች ይወድማሉ!

የማርክሲስት—ሌኒንስቶች ህብረት ይጠነክራል!

የወዛደሩ ፓርቲ ይመሰረታል!

የነፃ፤ የተደራጀና የታጠቀ ህዝብ አመጽ ያሸንፋል!